የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ሚያዝያ 12 ቀን 2001 ዓ.ም

ለአርቲስት ዶ/ር ጥላሁን ገሠሠ ቤተሰቦች
<u>አዲስ አበባ</u>

የአርቲስት ዶ/ር ጥላሁን ገሠሠ ዜና ዕረፍትን በሚመለከት የተሰማኝን ጥልቅ ሃዘን ስገልፅ በታላቅ አክብሮት ነው:: አርቲስት ዶ/ር ጥላሁን ገሠሠ የኢትዮጵያን ሙዚቃ ለመላው ዓለም በማስተዋወቅ ረገድ በህይወት ዘመኑ ላበረከተው አስተዋጽኦ አገራችን በእጅጉ ከምትኮራባቸው ስመጥር ሰዎች ዘንድ የሚቆጠርና በአገራችን ሙዚቃ ዕድገት ላይ ቀዳሚና ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ታላቅ ሰው ነው::

አርቲስቱ በህይወት ዘመኑ ለአገር በጐ አሳቢ፣ ለኢትዮጵያ ልማትና ዕድገት በዘርፉ የሚጠበቅበትን ሚና የተጫወተ አንጋፋ ሰው ነው:: አርቲስቱ በህይወት ዘመኑ ያበረከተው አስተዋጽኦ ለሌሎችም አርቲስቶች አርአያ መሆን የሚገባው ነው:: ለአርቲስቱ ቤተሰቦችና ዘመድ ወዳጆች መፅናናትን እመኛለሁ::

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት
Office of the Prime Minister